# ውሀ ለሰው፣ ለእንስሳት እና ለአትክልቶች ሂወት ነው፡፡ ለመንገድ ግን ማርከሻ መድሀኒት የሌለው መርዝ ወይም ካንሰር ነው፡፡

ይድረስ ለክቡር አቶ ድሪባ ኩማ የአዲስ አበባ አስተዳደር ከንቲባ እና ሌሎች የሀገራችን ከተማ አስተዳደሮች!!

በፍስሀ ገመዳ Fishageda@gmail.com 05-17-17

ከልጅነታችን ጀምሮ ስንማር ውሀ ከ80% በላይ የሰውነታችን ክብደት በላይ እንደሚሸፍን እና ያለውሀ መኖር እንደማንችል የተማርን ሲሆን ስናድግ ደግሞ ቢያንስ ሁለት ሊትር በቀን ውሀ መጠጣት ለጤናችን ወሳኝ መሆኑን በጤና ባለሙያዎች ተመክረናል፡፡ ለእፅዋትና እንስሳትም በተመሳሳይ ውሀ ለመኖር፣ ለማደግ እና ለመራባት እጅግ አስፈላጊያቸው ነው፡፡ እንዲሁም አንድ አከባቢ ለሰዎች፣ ለእፅዋትና ለእንስሳት ምቹ እንዲሆን በማድረግ ውሀ ወሳኝ ነው፡፡ በአጠቃላይ እፅዋትና እንስሳት ሰውን ጭምር ያለውሀ ከጥቂት ቀናት በስተቀር መኖር አይችሉም፡፡

እላይ ከተገለፀው በተቃራኒ ግን ውሀ ለመንገድ ገዳይ መርዝ ነው ወይም የመንገድ እድሜ እንዲያጥር የሚያደርግ ካንሰር ነው፡፡ የዚህ የመንገድ መርዝ ወይም ካንሰር ግን ማርከሻው ቀላል ነው፡፡ እሱም ክትትልና ትኩረት መስጠት ነው፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ ባለፉት አመታት ከሰራቻቻቸው እጅግ በርካታ ስኬታማ ስራዎች መካከል መንገድ አንዱ ነው፡፡ ከ20 አመታት በፊት እንደብርቅ ይታይ የነበረው የአስፋልት መንገድ በሁሉም የሀገሪቱ አከባቢዎች እየተዳረሰ ይገኛል፡፡ ለዚህ ደግሞ እኔ ራሴ ህያው ምስክር ነኝ ምክንያቱም በስራ አጋጣሚ በሁሉም ክልሎች ሊባል በሚችል ሁኔታ ተንቀሳቅሼ አይቻለሁ፡፡

ይህ ስራ ሳይደናቀፍ በዚሁ ከቀጠለ አገራችን ለወደፊቱ የአስፋልት መንገድ ሳይሆን የጠጠር መንገድ ብርቅ የሚሆንባት አገር እንደምትሆን የሚያጠራጥር አይሆንም ፡፡ በዚህ ለውጥ ደግሞ በሀገሩ መልማት ለሚኮራ ዜጋ ትልቅ ለውጥ ነው፡፡

በዚህ በመንገድ ልማት ዘርፍ ትልቅ ለውጥ ከተመዘገበባቸው መካከል ደግሞ አዲስ አበባ ከተማችን አንዷ ነች፡፡ አዲስአበባችን የቀለበት መንገዶች፣ የቦሌ እና የሌሎችም ሰፋፊ እና እጅግ ዘመናዊ አደባባዮች፣ የብሄር ብሄረሰቦች አደባበይን ጨምሮ በርካታ መንገዶች ተሰርቷል፡፡

ከዘመናዊ የአስፋልት መንገድ በተጨማሪ በአለማችን ዘመናዊ የሆነው ኤለክትሪክ የሚጠቀም ባቡር መስመር በመዘርጋትና ጥቅም ላይ በማዋልም አለምን አስደንቃለች፡፡ ምክንያቱም በብዙዎች እምነት ሀገራችን እንደሶማሊያ፣ ኤርትራ፣ ሱዳን፣ ኮንጎ፣ የመን፣ሶርያ፣ ወዘተ የጦርነትና የርሀብ ሀገር እንጂ ልክ የበለፀጉ ሀገራት እንደሚያደርጉት የረጅም ጊዜ ሰፋፊ እቅድ አውጥታ እሱንም ለመተግበር የምትችል አገር አድርገው አይቆጥሯትም፡፡ ለዚህም ነው ሀገራችን የባቡር መንገዱ ስራ ሲጀምር ልክ አንድ ቤተሰብ ህፃን ልጁ በእግሩ መሄድ ሲጀምር ብራቮ ብሎ እንደሚያጨበጭብ ሁሉ

ኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያ ወዳጆችም ያጨበጨቱ፡፡ በእርግጥ አንዳንድ የሀገር ውስጥና የውጭ ጠላቶች ከፍቷቸዋል፤ ምክንያቱም ከውድቀቷ እንጂ ከእድገቷ የሚጠቀሙ የማይመስላቸው እርኩስ መንፈስ የተጠናወታቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያን፤ ትውለደ ግብፃውያን፤ ትውልደ ሱማልያውያን፤ ትውልደ ኤርትራውያን ትውልደ አሜሪካውን ሞልቷልና፡፡

እንግዲህ ወደ ተነሳሁበት ሀሳብ ልመለስ እና ለተከበሩ ከንቲባችን መፃፍ ያነሳሳኝ አዲስ አባባ ከ26 አመት በላይ የማውቃት እና የምመላለስባት ቢሆንም የከተማዋ ነዋሪ መሆን ከጀመሪኩኝ ግን አራት አመት ሆኖኛል በመሆኑም በጣም እጅግ በርካታ ለውጦች እየተመዘገቡባት ያለች ከተማ መሆኑዋን ደግሞ በደንብ ከሚገነዙብት ውስጥ ራሴን  እመድባለሁኝ፡፡  አዲስ አበባ በእርስዎ አመራር ሰጭነት እና ከእርስዎ በፊት በነበሩ ከንቲባዎች እጅግ በርካታ መንገዶቸ ተሰርቷል፡፡ የጠፉ መንገዶች እንዳሉ የሚወራውም ሳንረሳ ማለቴ ነው፡፡

እነዚህ በርካታ መንገዶች እጅግ ውድ በሆነ ዋጋ እንደ ሚባለው ከሆነ አንዳንዶቹ መንገዶች ለአንድ ኪሎሜትር ሀምሳ ሚሊዮን ብር በኪሎሜትር የተሰሩ እጅግ ውድ መንገዶች ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ ሊበራታ የሚገባው ትክክለኛ መንገድ ነው፡፡ ምክንያቱም በየጊዜው እያፈረሱ በመገንባት ገንዘብና ጊዜ እንዲባክን ከማድርግ ዘመን ተሻጋሪ፤ ለትውልድ የሚተላለፍ ደረጃውን የጠበቀ ስራ መስራት ተመራጭ ነው፡፡  በመሆኑም የከተማ አስተዳደሩ ሊመሰገን ይገበዋል፡፡ በተጨማሪም በእርስዎ ጊዜ የታዘብኩት ለውጥ ከተማዋ የድንጋይ ክምር ናት (ህንፃ ብቻ ናት) ስትባል የነበረውም ቢሆን አሁን በመንገድ ዳር ችግኝ በማስተከል በተወሰነ ደረጃም ቢሆን አረንጓዴ ተክል እንዲኖራት ማድረግዎ ትልቅ ምንስጋና አለኝ፡፡ ነገር ግን በብዙ ቦታዎች የተተከሉ ችግኞች የሉም ምክንያቱም አንዳንዱ ሰው ሆን ብሎ ያጠፋቸዋል፤ አንዳንዱ ደግሞ በእንክብካቤ እጦት ውሀ አጥተው ይጠፋሉ፡፡ ስለሆነም ከተተከሉ አይቀር ቁጥጥር የሚያደርግ ተንከባካቢ እነዲኖራቸው እና የተመደቡት ደግሞ በችግኞች ብዛት የሚከፈላቸው ቢሆን፤ ከጠፉ ተጠያቂ የሚሆኑበት መንገድ ቢኖር መልካም ይሆናል እያልኩኝ ዛሬ ለመጻፍ የተነሳሁት ግን ከመንገድ ጋር በተገናኘ ያለው ችግር ነው፡፡

## መንገድ በአዲስ አበባ

እንግዲህ አዲስ አበባ እንደሚባለው ከሆነ ከ80% በላይ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የሚንቀሳቀስባት፤የሀገራችን እና የአፍሪካ መዲና እንዲሁም የበርካታ አለም አቀፍ ድርጅቶች መቀመጫ እና ከአንዳንዶቹ የሀገራችን ክልሎችም የበለጠ የህዝብ ብዛት ያላት አዲስ አበባ እየተሰሩላት ያሉት መሰረተ ልማቶች ይበል የሚያስብል ከመሆኑም በላይ ከዚህ በላይ ሊሰራላት  ይገባል፡፡ ነገር ግን መስራት ብቻ ሳይሆን የተሰሩትንም መንከባበከብ መከታተል ያስፈልጋል፡፡

አንድ አርሶ አደር እርሻውን ከዘራ በኃላ አረም ወይም ተባይ እንዳያጠፋበት ይከታተላል ያርማል፤ ፀረ ተባይ መድሀኒት ይረጫል ይንከባከባል፡፡

አንድ ወታደር( መከላከያ) ጠላት ሀገር ውስጥ ገብቶ ጥቃት እንዳያደርስ ቀን ከሌሊት በንቃት ይጠብቃል፡፡ ደህንነቱም እንደዚሁ ሰርጎገቦች ሀገር ውስጥ ገብተው ጥፋት እንዳያደርሱ መነሻቸው ድረስ በመሰለል እቅዳቸውን ያከሽፋል፤ ፖሊስም እንዲሁ የህዝቡን ሰላም ለመጠበቅ የሚቻለውን ያደርጋል፤ በተለይም ስብሰባ ሲካሄዱ ልዩ ጥበቃ እና ክትትል ያደርጋል እንቅልፍ የለም፡፡ ይህ በመሆኑም በሀገራችን እጅግ በርካታ አህጉራዊና አለም አቀፋዊ ስብሰባዎች በሰላም ተካሂዷል ለወደፊቱም ይካሄዳሉ፡፡

የጤና ሚንስትርም መከላከልን መሰረት ያደረገ የጤና ፓሊሲ በመተግበር ሀገራችን ምንም እንኳ አመጋገባችን እና አኗኗራችን ለተለያዩ በሽታዎች ተጋላጭ ቢያደርገንም እስከአሁን የከፋ ሁኔታ እንዳይከሰት እና የህዝባችን ጤንነት እየጠበቀ ይገኛል፡፡

የመንገድ ባለስልጣን ከነዚህ ሀይሎች ምን መማር አለበት፣ የሰራው መንገድ ጎርፍ እንዳይበላው እና ሀገሪቱ እንዳትከስር መከታተል ይገቧል እንቅልፍ ሊወስደው አይገባም፡፡ መንገዶች ፈርሰው፣ ወይም ተበላሽተው፣ ህዝቡም ተሰቃይቶ ክረምት ካለፈ በኃላ እጅግ በርካታ ገንዘብ እያወጣ ከሚጠግን መጀመሪያ እንደ ደህንነቱ፣ ወታደሩ፣ ወይም ፖሊሱ አደጋ እዳይመጣ ሌት ተቀን እንደሚሰራው ተጋላጭ የሆኑትን አከባቢዎች በማጥናት ቅድመ መከላከል ከጤና ሚንስቴር ይማር፡፡ ውሀ መንገዱን ከቦይ ወጥቶ ወደ ዋናው መንገድ ገብቶ ሲሄድ ዝምብሎ አይመልከት ልክ እንደ እሳት አደጋ ቶሎ ደርሶ ወደ ቦታው ይመልስ ወዘተ፡፡

ታሞ ከመማቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ የሚለው መርህ በመንገዱ ሴክተርም መንገድ ተበላሽቶ ወደጥገና ከመሮጥ ከመበላሸቱ በፊት ጥንቃቄ ያድርግ፡፡ እጅግ በርካታ ወጭ ለጥገና ከሚያወጣ ብዙ ስራአጥ ወገኖችን በየአከባቢው በመቅጠር ቱቦዎች እንዳይደፈኑ፣ ክረምት ሲገባ ውሀ ወደመንገድ እንዳይገባ የዝናብ ልብስ ለብሰው የሚከታተሉ ወጣቶችን ቀጥሮ ያሰራ፡፡ ይህ ደግሞ በዘፈቀደ ሳይሆን በየአከባቢው ሁኖ መንገዱ ተለክቶ መስጠት፣ ካለበለዚያ አንዳንድ ቦታ ለፅዳት ተቀጥረው  ቆሻሻ የሚያነሳው አጥቶ እንደሚቀመጠው ይሆናል፡፡

አስቲ ብዙ ትምህርት የማይጠይቅ ከሶስት ቀን በፊት በዚሁ ፎረም ያካፈለኳቹህን ቦታዎች በሀሳብ ላስቃኛቹህ እና የተወሰኑ ከዚህ በታች ያሉትን ፎቶዎችን ተመልከቱ፡፡

ከጎተራ ወደ መስቀል አደባባይ በሚወስደው መንገድ ከላንቻ ጀምራቹህ ተመልከቱት ፡፡

1. ላንቻ ወይም ኮንኮርድ ሆቴል ሁናቹህ ወደ ሰሜን መስራቅ ስትመለከቱ ወደ ላንቻ ፓሊስ ጣብያ፣ ዩኒሴፍ መጋዘን ወዘተ የሚወስድ መንገድ አለ፡፡ ይህ መንገድ ረጅም ሲሆን ከዚህ መንገድ የሚመጣ ውሀ እንዳለ ከነ አፈሩ፣ድንጋዩና ቆሻሻው ወደ ዋናው መንገድ ይዞት ይገባል፡፡ ዋነው መንገድ እና ጠባቡ መንገድ መገናኛ ላይ የብረት ርብራብ አለ ይህ ደግሞ ከፎቅ የሚንጠፋጠፍ ውሀ ያስተላለፍ ካልሆነ በስተቀር ቆሻሻና አፈር የሚመጣ ውሀ ያውም ከዳገታማ/ከፍ ካለ ቦታ ከነቆሻሻው የመጣ ውሀ ሊያስተላልፍ አይችልም ይህ ለመገመት የሚያይ አይን እና ጤነኛ ጭንቅላት ብቻ በቂ ነው፡፡

2. ከላንቻ አለፍ ስትሉ የቤሎስ ኬክ ቤት ማዶ በኦሮሚያ ፖሊስ ጎን እንደዚሁ ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ ረጅም የውስጥ ለውስጥ መንገድ አለ፡፡ ይህ መንገድም ውሀውን እንዳለ ከነቆሻሻው ይዞ ወደዋናው መንገደ በመግባት የባቡሩ መንገድ ጠርዝ ሳይቀር እየቦረቦረው የሚገኝ ሲሆን ከባቡር የሚወርድ ወይም ለመሳፈር የሚንቀሳቀስ ሰው እንቅስቃሴ ሲገድብ ይታያል፡፡

3. ግሎባል ሆቴል በግራና በቀኝ ያሉት ጠባብ መንገዶች በጣም ተዳፋታማ ከመሆናቸው በተጨማሪ ረጃጅም ናቸው መንገዶች እንዳለ ውሀቸውን ከነአፈራቸው ወደ ዋናው መንገድ ይለቁትና የአስፋልቱን መንገድ ሙሉ በሙሉ በሚባል ይሸፍኑትና አንዳንዴ መኪኖችም ለማለፍ ይቸገራሉ፡፡ ውሀው አስፋልቱን ሞልቶ የባቡር መንገዱ ጥግ ጥግ እስከ ሰናይ ክሊኒክ ወደ ደቡብ አቅጣጫ  ሂዶ ጎተራ አከባቢ ያለው ዝቅተኛ/ ረባዳ ቦታ ይገባል፡፡

4. በቅሎ ቤት ያለው የገቢዎች ቢሮ ወደ ስሜን ምስራቅ የሚያስገቡ ግራና ቀኝ መንገዶች

5. ከበእምነት ምግብ ቤት እና በነዳጅ ማደያው መሀል ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ ያለው መመንገድ

እነዚህ ሁሉ መንገዶች ልክ እንደ ገባር ወንዞች በሙሉ ወደ ዋናው አስፋልት ይለቁት እና አሰፋልቱን ብቻ ሳይሆን የባቡር መንገዱንም ጥግ ጥግ እየቦረቦሩ ይሄዳሉ እናም እጅግ በርካታ ገንዘብ ወጥቶበት በውጭ ባለሙያዎች ድጋፍ የተሰራው መንገድ ከጥቅም ውጭ እየሆነ ይገኛል፡፡

6. ከኤግዚብሽን ማእከል የጓሮ በር ወይም የምስራቅ አቅጣጫ ተነስቶ ወደ ዋናው መንገድ እየተንደረደረ ያለምንም ክልካይ ከሳሪስ በኩል መስቀል አደባባይ (ኦረሚያ የባህል ማእከለ) አከባቢን ካጥለቀለቀ እና እጅግ ውብ የነበረውን መንገድ ከተጫወተበት በኃላ ያለማንም ከልካይ ወደ መሀል ዋናው የመስቀል አደባባይ አሰፋልት ይነጉዳል፡፡ ይህ እንግዲህ ከሁሉም በጣም የሚያሳም ነው፡፡ ምክንያቱም የሀገሪቱ መሪዎች ሳይቀር የሚመላለሱበት መንገድ ነው መቸም ሳያዩት ይቀራሉ ተብሎ አይታሰብም  ምናልባት ማየትና መስተዋል ካልተለያዩ በስተቀር፡፡

7. ሌላው ባለፈው አመት በከፍተኛ ወጭ የተሰራው እና አንድ ክረምነት እንኳ ሳያልፍ በገጠሪቱ የሀገራችን ክልለች እንደሚሰሩት ውሀ ማቆርያ (ኩሬ) አይነት በልደታ ባልቻ አከባቢ ያየሁትን ነው፡፡ ይህ ቦታ ወደ ምሲኮ፤ ቄራ፤ አብነት ወዘተ ታክሲ መያዣ ሲሆን እጅግ በርካታ መኪኖች የሚተላለፉበት ሰሆን በአከባቢው የኢትዮጲያ ንግድ ባንክ ባልቻ ቅርንጫፍ፤ አባይ ባንክ ልደታ ቅርንጫፍ፤ ቡና ባንክ ወዘተ የሚገኙበት ነው ይህ መንገድ ከመክሲኮ አቅጣጫ ወይም ቅዱስ ጊያረጊስ ቢራ አቅጣጫ ያለው መንገድ እና ሌሎች አራቱም አቅጣጫ የሚመጣው ውሀ መገኛው ላይ በመተኛት አመት ያልሞላው መንገድ ልክ በአፈር የተሰራ ኩሬ አስመስሎት ይታያል እናም የሚተላለፉት ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ መኪኖችም ተቸግሯል፡፡ እሲተ ለዛሬ በልደታ በ7/9/2009ዓ.ም በስልኬ የነሳሁትን ፎቶ ላካፍላቹህ፡፡

የዚህ ፅሁፍ አላማ የሚመለከተው አካል ችግሮችን ምናልባት ካልተገነዘባቸው ቢያያቸው ነው፡፡ ሀገርን እየቀየረ ያለው አመራር እና መንግስት ስራዎችን ለማንኳሰስ ሳይሆን የበለጠ የሚጠናከሩበትን መንገድ ለመጠቆም ነው፡፡  ሌሎች ክልሎችም ከሀዋሳ ከተማ ሊማሩ ይገባል እያልኩኝ በቀጣይ ለኬንያ፤ ደቡብ አፍሪካ እና ሌሎች አፈሪካውያን ሀገራት ምሳሌ በመሆን በአፍሪካውን መነቃቃትን የፈጠረው የአዲስአበባችን የባቡር መንገዳችን የታዘብኳቸውን እና ሊታረሙ ይገባሉ የምላቸውን ሀሳቦች እሰነዝራለሁ፡፡ ምክንያቱም ተክል በችግኝነቱ፤ ሰው በልጅነቱ፤ ቆዳም እንዲሁ በእርጥቡ እንደሚባለው የባቡር አገልግሎታችናነ አመራሩ ልክ እንደ አየር መንገዳችን ተምሳሌት ሆኖ እንዲወጣ ሁሉም ከአሁኑ የሚያያቸውን በመጠቆም ልናስተካክለው ይገባል፡፡ መሪዎቻችንም ካለችን ትንሽጊዜ እና እውቀት ተነስተን የምናነሳቸው ሀሳቦች ሳይንቁ ሊያይዋቸው፤ ሊገመግሟቸው እና ለሀገር ግንባታ የሚጠቅሙትን ሊወስዱ ይገባል እላለሁ፡፡

ኢትዮጵችን በክብርና በብልፅግና ለዘለአለም ትኑር!!!!!



ልደታ ባልቻ ሆስፒታል አከባቢ፡፡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ባልቻ ቅርንጫፍ ፊት ለፊት ከአራቱም አቅጣጫ የሚመጣው ውሀ የሚተኛበት መስቀለኛ መንገድ፡፡

